............ቀን 2009 ዓ.ም.

የውክልና ሥልጣን ማስረጃ

**ወካይ**፡ ወ/ሮ/ት አቶ..............፣ ዜግነት....... ፓስፖርት/መታወቂያ ቁጥር ...............

**አድራሻ**፡ ............................

**ተወካይ**፡ አቶ/ወ/ሮ/ት ..............፣ ዜግነት ኢትዮጵያዊ

አድራሻ፡ አዲስ አበባ፣ ነፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 2፣ የቤት ቁጥር ....

እኔ ወካይ ለተወካይ የምሰጠው የውክልና ስልጣን ተወካይ እንደ እኔ በመሆን የልደት ሰርቲፊኬቴ እንዲያወጡልኝ፣ እንዲያረጋግጡልኝ፡ እንዲሁም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና አዲስ አበባ በሚገኘው የኔዘርላንድ ኤምባሲ እንዲያረጋግጡልኝ፣ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ክፍያዎች እንዲከፍሉ እና አስፈላጊውን ሁሉ እንደ እኔ በመሆን እንዲፈጽሙልኝ ይህንን የውክልና ሥልጣን ማስረጃ የሰጠኋቸው መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የወካይ ፊርማ :--------------------

ከዚህ በላይ የሰፈረው ፊርማ ወ/ሮ/ት አቶ............... ኤምባሲው ድረስ በአካል በመቅረብ የፈረሙት መሆኑን ኤምበሲው ያረጋግጣል፡፡

................ ቀን 2009 ዓ.ም

## የውክልና ሥልጣን ማስረጃ

ወካይ: አቶ-ወ/ሮ/ት........................ ዜግነት ኢትዮጵያዊ/ት ፓስፖርት/መታወቂያ ቁጥር ......

አድራሻ: ..............................

ተወካይ: ወ/ሮ/ት-አቶ .......................፣ ዜግነት ኢትዮጵያዊ/ት

አድራሻ: ..................................(ከተማ፣ ክፍለ-ከተማ፣ ወረዳ፣ ቀበሌ፣ የቤት ቁጥር.)

እኔ ወካይ ለተወካይ የምሰጠው የውክልና ስልጣን በሀገር ውስጥ በነበርኩበት ወቅት እጠራበት የነበረው ስም .................... ሲሆን በአሁን ሰዓት በውጭ አገር ሲኖር እየተጠቀምኩበት ባለመሆኑ ..................ተብዬ ለመጠራት እንድችል ዘንድ የስም ለውጡን በህጋዊ መንገድ ፍርድ ቤት ቀርበው እንዲያፀድቁልኝ፤ በፍርድ ቤት የፀደቀውን የስም ለውጥ በማድረግ የልደት ሰርቲፊኬት እንዲያወጡልኝ፣ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና በኔዘርላንድ ኤምባሲ አረጋግጠው እንዲልኩልኝ፣ ቃለ-መሃላ እንዲፈጽሙ፤ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የህግ ባለሙያ ቀጥረው/ወክለው የፍርድ ቤት ጉዳዮችን እንዲያስፈጽሙ፡ ይህንን የውክልና ስልጣን የሰጠኋቸው መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ::

የወካይ ፊርማ:- --------------------

ከዚህ በላይ ያለው ፊርማ አቶ-ወ/ሮ/ት............ኤምባሲው ድረስ በግንባር በመቅረብ የፈረሙት መሆኑን ኤምባሲው ያረጋግጣል::

.................. ቀን 2009 ዓ.ም.

## የውክልና ሥልጣን ማረጋገጫ

ወካይ: አቶ/ወ/ሮ/ት................... ፣ ዜግነት:ኢትዮጵያዊ/ት ፓስፖርት/መታወቂያ ቁጥር..............:

አድራሻ: ......................................................

ተወካይ: አቶ/ወ/ሮ/ት.........................፣ ዜግነት: ኢትዮጵያዊ/ት

አድራሻ: ...................................................( ከተማ፣ወረዳ...፣ ቀበሌ... ፣የቤት ቁጥር .......)

እኔ ወካይ ለተወካይ የምሰጠው ውክልና ተወካይ የጡረታ አበሌን ከዚህ በፊት እንደሚቀበሉልኝ ሁሉ በቀጣይም እንዲቀበሉልኝ እና ከዚሁ ጋር በተያያዘ አስፈላጊውን ሁሉ እንደኔ ሆነው እንዲፈጽሙና እንዲያስፈጽሙ የውክልና ሥልጣኑን በፍ/ብ/ህ/ቁ 2199 መሠረት ያራዘምኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ::

የወካይ ፊርማ

ታደሠ ጃራ ጩበታ

ከዚህ በላይ የሰፈረው ፊርማ አቶ- ወ/ሮ/ት..............ኤምባሲው ድረስ በግንባር በመቅረብ የፈረሙት መሆኑን ኤምባሲው ያረጋግጣል::

............ ቀን 2009 ዓ.ም

## የውክልና ስልጣን ማስረጃ

ወካይ፡ ወ/ሮ/ት አቶ ..........፣ ዜግነት ኢትዮጵያዊ/ት፣ፓስፖርት/መታወቂያ ቁጥር ..................

አድራሻ: ..................................................

ተወካይ፡ ወ/ሮ/ት ............፣ ዜግነት ኢትዮጵያዊ/ት

አድራሻ: አዲስ አበባ፡ ......... ክ/ከተማ፣ ወረዳ ....፣ የቤት ቁጥር .......

እኔ ወካይ ለተወካይ የምሰጣቸው የውክልና ስልጣን በአዲስ አበባም ሆነ በክልሎች ከተሞች በስሜ ተመዝግቦ የሚገኘውን፣ማንኛውም የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት እንዲያስተዳድሩ፣ እንዲጠብቁ፣ እንዲቆጣጠሩ፣ውል እንዲዋዋሉ፣ ስም እንዲያዛውሩ፣ እንዲያከራዩ፣ እንዲያኮናትሩ፣ በስሜ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት (ቤትም ሆነ መኪና) መግዛት እንዲችሉ፣ በስሜ ካርታ፡ ፕላን፣ የባለቤትነት ደብተርንና ሊብሬ አሰርተው መረከብ እንዲችሉ፣የግንባታ ፈቃድ እንዲያወጡ፣በሥሜ በማህበር ተደራጅተውም ሆነ በግል በሊዝ ቦታ እንዲመሩ፣ በስሜ ድርጅት በአዲስ አበባም ሆነ በክልል ከተሞች እንዲሁም በገጠር እንዲያቋቁሙ፣ ድርጅቱ እንዲያስተዳድሩ፣ ድርጅቱ በተመለከተ የሚፈለገው ተግባራት እንዲያከናውኑ፣ ድርጅቱ በተመለከተ ከመንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ የግል ድርጅቶች ህጋዊ የስራ ግንኙነት እንዲደደርጉ፣ ንብረት እንዲረከቡ፣ የግንባታ ፈቃድ እንዲያወጡ፣ የግንባታ እቃዎች /ሲምንቶ... ወዘተ / እንዲገዙ፣ የግንባታ ሥራ ባለሙያ ቀጥረው ቤት እንዲያሰሩ፣ ውል እንዲያሻሽሉ፣ እንዲያድሱ፣ በውሃና ፍሳሽ፣ በመብራት ኃይልና በቴሌኮም መ/ቤት ውል ተዋውለው ውሃ፣ መብራትና ስልክ እንዲያስገቡ፣ ግብር እና የሚከፈሉ ክፍያዎችን እንዲከፍሉ፣ ገንዘብና ሰነድ እንዲቀበሉ፣ እንዲሰጡ፣ በስሜ ከውጭ ሀገር ተመዝግቦ የሚመጣ መኪናም ሆነ እቃ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን አስፈላጊውን ፕሮሰስ አሟልተው እንዲረከቡና ተገቢውን ተግባር እንዲፈጽሙ፣ ቀረጥ እንዲከፍሉ፣ ቦሎና ከላውዶ እንዲያስደርጉ፣ ሰሌዳ ማስቀየር እንዲችሉ፣ በስሜ የንግድ ፈቃድ ከሚመለከተው አካል እንዲያወጡ፣ የንግድ ፈቃዱ መቀየረም ሆነ መመለስ እንዲችሉ፣ ሲፒኦ እንዲያሲዙ፣ ኢንሹራንስ እንዲገቡ፣ በስሜ ጨረታ እንዲጫረቱ፣ የጨረታ ሰነድ እንዲገዙ፣ አክሲዮን እንዲያቋቁሙ፣የአክስዮን ድርሻዬ ገንዘብ እንዲቀበሉ፣አክሲዮን እንዲሸጡና እንዲለውጡ፣ ከወረዳው ጽ/ቤት መታወቂያ እንዲያወጡልኝ፣ በስሜ የአደራ ደብዳቤ እንዲቀበሉ፣ አስፈላጊውን ሁሉ እንዲያከናውኑ፣ ሌሎች የሚያስፈልጉኝን ሰነዶች ከማንኛውም ቦታ አውጥተው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና አዲስ አበባ በሚገኘው ኔዘርላንድ ኤምባሲ እንዲያረጋግጡልኝ፣ በአጠቃላይ እንደኔ ተጠሪ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ፣ በስሜ በማንኛውም ባንኮች የሂሳብ አካውንት እንዲከፍቱ፣ ገንዘብ ገቢና ወጭ እንዲያደርጉ፣የሚከፈሉ ክፍያዎችና ግብር እንዲከፍሉ፣ ቼክ ፈርመው መስጠትም ሆነ መቀበል እንዲችሉ፣ ማንኛውንም ዶክመንቶች ከማንኛውም ቦታ ቀርበው ሰነድ ላይ ፈርመው እንዲቀበሉ፣ የሚከሰሱበትም ሆነ በሚከስበት ሁሉ ጠበቃ ቀጥረው እንዲከራከሩ፣ ቃለ ማሀላና ማረጋገጫ ላይ እንዲፈርሙ፣ መልስና የመልስ መልስ እንዲሰጡ/እንዲቀበሉ፣ ውሳኔ እንዲፈፅሙ፣ይግባኝ እንዲጠይቁ፣ በክልሎች፣ በአዲስ አበባ አስተዳደር ክፍለ ከተሞች፣ በወረዳዎች፣ በቀበሌዎች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በቤቶች ኤጀንሲ፣ በውጭ ጉዳይ ሚንስቴር፣ በኢንቨስትመንት ቢሮ፣በንግድ ሚንስቴር፣ በኢሚግሬሽን፣ በቴሌኮም መ/ቤት፣ በፖስታ ቤት፣ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት፣ በመንገድ ትራንስፖርት፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ... ወዘተ በአጠቃላይ በማናቸውም መንግስታዊና ህዝባዊ ድርጅቶች በመቅረብ የኔ ጉዳዮች እንዲፈጽሙና እንዲያስፈጽሙ፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ሶስተኛ ወገን እንዲወክሉ፣ ይሄንን ሙሉ የውክልና ስልጣን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2199/2205/58 መሰረት መስጠቴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

የወካይ ፊርማ ..................................

ከዚህ በላይ የሰፈረው ፊርማ ወ/ሮ/ት ............... ኤምባሲው ድረስ በአካል በመቅረብ የፈረሙት መሆኑን ኤምበሲው ያረጋግጣል።

………ቀን 2008 ዓ.ም.

# የውክልና ስልጣን መሻርያ

የውክልና ሻሪ ስም፡ አቶ-ወ/ሮ/ት ………… ፣ ዜግነት ኢትዮጵያዊ/ት ፓስፖርት/መታወቂያ ቁጥር ….

**አድራሻ** : ………………………………………

የውክልናው ተሻሪ ስም፡ አቶ- ወ/ሮ/ት ………… ፣ ዜግነት ኢትዮጵያዊ/ት

አድራሻ፡ ………………………………

እኔ የውክልና ስልጣን ሻሪ ህዳር 16 ቀን 2002 ዓ.ም በኢትዮጵያ ኤምባሲ ብራስልስ ቀሪቤ ለም/ኮማንደር ሙሉጌታ ለገሠ የሰጠኃቸውን የውክልና ስልጣን ከዛሬ ሐምሌ 11 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2226 መሠረት የሻርኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የውክልና ሻሪ ፊርማ፡ ………………

ከዚህ በላይ የሰፈረው ፊርማ አቶ-ወ/ሮ/ት………………….ኤምባሲው ድረስ በአካል በመቅረብ የፈረሙት መሆኑን ኤምበሲው ያረጋግጣል፡፡